# ኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

## የቅጅ መብት ሮያሊቲ (የአገልግሎት ክፍያ) ተመን አወሳሰን መመሪያ

**643/2013**

አዲስ አበባ
የካቲት 2011

## <u>መግቢያ</u>

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከተቋቋመበት ዓላማ አንዱ የኮፒራይት ኢንዱስትሪውን መደገፍ እና የቅጅና ተዛማጅ መብቶች የጋራ አስተዳደር ማህበራት ወደ ተግባር የሚገቡበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን መዘርጋት ነው፤

ስለሆነም የጋራ አስተዳደር ማኅበራት ለጽ/ቤቱ የሚያቀርቡት የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ረቂቅ በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 2(30) እና በማሻሻያ አዋጅ ቁ/872/2007 አንቀፅ 2(1) ላይ ጥበቃ ያላቸው ሥራዎች ለሀገር የሚያበረክቱትን ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሚና የሚያማዝ፣ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ እና የተጠቃሚዎችን ዓቅም ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ስለሚገባው፤

በመሆኑም በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 872/2007 አንቀጽ 34(2) መሰረት ጽ/ቤቱ በጋራ አስተዳደር ማህበራት ተዘጋጅቶ የሚያቀርብለትን የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ረቂቅ እንደሚያፀድቅ የሚደነግግ ሲሆን ይህንንም ለመወሰን በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 39(2) በተሠጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ በጋራ አስተዳደር ማህበር የሚዘጋጅ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ማሟላት የሚጠበቅበትን ጉዳዮች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 643/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

   1. "ስምምነት" ማለት የጋራ አስተዳደር ማህበር እና ተጠቃሚዎች የሮያሊቲ ክፍያ ተመንን በተመለከተ ድርድር ካደረጉ በኋላ የሚያቀርቡት ውል ነው።
   2. "ውስን ተመን" ማለት የሮያሊቲ ክፍያ ተመን በሚወሰንበት ጊዜ የአገልግሎት መስጫ ተቋም የተቋቋመበት ቦታ ስፋት፣ አገልግሎቱ የሚሰጥበቸው ክፍሎች ብዛት፣ የአካባቢው መገኛ ሁኔታ፣ የሚሸጠው አገልግሎት ዋጋ እና መሰል ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚተመን የተመን ዓይነት ነው።

3. "የንፅፅር ተመን" ማለት ሥራን በሚያባዛ፣ በመድረክ ለሕዝብ ዕይታ በሚያቀርብ፣ በቋሚነት ወይም አልፎ አልፎ በኮንሰርት ወይም መሰል ጉዳዮች መልክ ለህዝብ ዕይታ በሚያቀርብ፣ በተንቀሳቃሽ ፊልም መልክ ለቤት ዕይታ በሚያከራይ፣ በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን በሚያስተላልፍ ተቋም ወይም ግለሰብ ላይ የሚተመን የተመን ዓይነት ነው።

4. "ሥራ ዘርፍ" ማለት የሮያሊቲ ክፍያን የሚፈጽሙ ተጠቀሚዎችን በየሥራው ዓይነት ለያይቶ ማቅረብ ማለት ነው፡፡

5. "ተጠቃሚዎች" ማለት በአዋጁ መሰረት ጥበቃ የሚያገኙ ስራዎችን ለንግድ ዓላማ በተያያዘ ጥቅም ላይ የሚያውል ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር አዘጋጅቶ በሚያቀርብ በማንኛውም የጋራ አስተዳደር ማኅበር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር አዘገጃጀት፣ አተማመንና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

4. የሮያሊቲ ቀመር ስሌት አዘገጃጀት

1) የሮያሊቲ ቀመር ስሌት በጋራ አስተዳደር ማህበር አማካይነት ይዘጋጃል፤
2) በጋራ አስተዳደር ማኅበር የሚዘጋጀው ረቂቅ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ተጠቃሚዎች ሥራው የሚያስገኝላቸውን ገቢ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፤
3) የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ረቂቅ በየሥራ ዘርፉ ተተንትኖና ተብራርቶ መዘጋጀት አለበት፤
4) በጋራ አስተዳደር ማኅበሩ እና በተቃሚዎች መካከል በተደረጉ ምክክሮች የተገኙ ውጤቶችና አስተያየቶች የያዘ መሆን ይኖርበታል፤
5) የሚዘጋጀው የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ለትምህርት አገልግሎት፣ ለባህላዊ እና ማህበራዊ ዕድገት፣ ለህዝባዊ አገልግሎቶች ልዩ ቅናሽ ማድረግ አለበት፤

5. የሮያሊቲ ቀመር ስሌት በሚዘጋጅበት ወቅት የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፤

ኤርሚያስ የማነብርሃን
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Intellectual Property Office

1) ሥራው ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዓላማ፣ ዓይነትና መንገድና መጠን፤

2) ሥራው ጥቅም ላይ የሚውልበትን የቦታ ስፋትና የወንበር ብዛት፤

3) ከተጠቃሚዎች ጋር በተደረጉ ምክክሮች የተገኘ ውጤትና አስተያየቶች፣

4) ተጠቃሚዎች ጥቅም ላይ የሚያውሉት የፈጠራ ሥራ የሚያስገኘው ገቢ፣

5) ተጠቃሚዎች ጥቅም ላይ የሚያውሉት የፈጠራ ሥራ ዓይነት፣ብዛት፤

6. የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ዘዴዎች፤

1) ከተጠቃሚዎች ጋር በሚደረግ ስምምነት የተመሰረተ ተመን፤

2) በውስን ተመን፤

3) በንፅፅር ተመን፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ቀመሩን ማስላት ካልተቻለ የተጠቃሚውን ዓመታዊ ገቢ በመቶኛ ታሳቢ በማድረግ የሮያሊቲ መጠን መወሰን ይቻላል፤

7. የሮያሊቲ ቀመር ማመልከቻ አቀራረብ

1. በሃገሪቱ የፌደራል መንግስት የሥራ ቋንቋ መሆን አለበት፤

2. የሚቀርበው ማመልከቻ

ሀ. ከተጠቃሚዎች ጋር የተደረጉ ምክክሮች፣ የተገኙ ውጤቶችና አስተያየቶችን የያዘ ሠነድ፣

ለ. ከተጠቃሚዎች ጋር የተደረገ የስምምነት ሰነድ፤

i. ስምምነቱን የፈፀሙት አካላት ዝርዝር፤

ii. ስምምነቱ የሚሸፍነው የጊዜ ስፋት፤

iii. ስምምነት ላይ የተደረሰበት የክፍያ መጠን፤

iv. ሌሎች በጽ/ቤቱ የሚጠየቁ ሰነዶች፤

8. ማመልከቻን ስለመመርመር

1. ጽ/ቤቱ በጋራ አስተዳደር ማህበሩ ተዘጋጅቶ የቀረበውን ረቂቅ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር በዚህ ዙሪያ ተፈፃሚነት ካላቸው ህጎች ጋር የሚጣጣም ሆኖ ካገኘው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አጽድቆ በጽሁፍ ያሳውቃል፤

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Intellectual Property Office

2. ጽ/ቤቱ የቀረበለት ረቂቅ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር በዚህ ዙሪያ ተፈፃሚነት ካላቸው ህጎች ጋር የሚጣረስ ሆኖ ካገኘው የጋራ አስተዳደር ማህበሩ በ15 ቀናት ውስጥ አሻሽሎ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ይሰጣል፤
3. ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተሻሽሎ ካልቀረበ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመሩ ተፈፃሚነት አይኖረውም፤

9. የሚዘጋጀው የሮያሊቲ ተመን

1. የተለየ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የተዘጋጀው የቀመር ተመን ለሦስት ዓመት ያገለግላል፤
2. አዲስ የሚዘጋጀው የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር በፊት ይሰራበት የነበረው ቀመር የጊዜ ገደቡ ከማለቁ 2 ወር በፊት ለጽ/ቤቱ መቅረብ አለበት፤

10. የሮያሊቲ ክፍያ ቀመሩ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

የፀደቀው የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሻሻል ይችላል፤

1) በጋራ አስተዳደር ማህበሩ ወይም በተጠቃሚዎች ጥያቄ መሠረት፤
2) ጽ/ቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነበት ጊዜ፤

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11. መረጃን ማሰራጨት

1. በጋራ አስተዳደር ማኅበሩ ተዘጋጅቶ የቀረበው የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ረቂቅ ለህዝብ አስተያየት ሠፊ ሽፋን ባለው በመገናኛ ብዙሃን መገለፅ አለበት፤
2. በጋራ አስተዳደር ማኅበሩ ተዘጋጅቶ የቀረበው የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር በጽ/ቤቱ ከጸደቀ በኃላ በአንድ ወር ውስጥ የጋራ አስተዳደሩ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት አለበት፤

Federal Democratic Republic of Ethiopia

## 12. ቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ስርዓት

1. በጋራ አስተዳደር ማህበሩ ተዘጋጅቶ የቀረበውን ረቂቅ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ላይ የሚቀረቡ ቅሬታዎችን በማጤን ጽ/ቤቱ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ ያዘጋጀውን የሮያሊቲ ተመን እንደገና እንዲመረምረውና ቅሬታዎችን እንዲመለከት ያዛል፤
2. የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የቀረቡትን ቅሬታዎች በመመርመር ተገቢውን ምላሽ በአንድ ወር ጊዜ ለፅ/ቤቱ ማቅረብ ይኖርበታል፤
3. በጋራ አስተዳደር ማኅበሩ እና በተጠቃሚዎች መካከል በሮያሊቲ ክፍያ ቀመር ዙሪያ መግባባት ላይ መድረስ ካልተቻለ በማሻሻያ አዋጁ አንቀጽ 44 መሠረት የሚዳኝ ይሆናል፤

## 13. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከካቲት 22 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ

ኤርሚያስ የማነብርሃን

ዋና ዳይሬክተር